

ሰ ን ደ ቅ ፡ ዓ ላ ማ ች ን ፤

# ምሁሮቻችንን ፡ ከማመስገን ፡ አንቆጠብ ፤

ከስለሺ ነህ ፡ ገላነህ ፣ ኩቤክ ፣ ካናዳ ፤

በየግዜው ፡ በሚጽፉቸውና ፡ ቆራጥ ፡ ኢትዮጵያዊነት ፡ መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ ከምናደንቃቸው ፡ አንዱ ፡ አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ረዳን ፡ በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ እያመሰግንን ፦

“Ibsaa Guutama’s Self Doubt Plunged Him to Swim Deep In to the Lake Hate” በሚል ፡ አርእስት ፡ ያተቱት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሆነ ፡ ቋንቋውን ና ፡ ተናጋሪውን ፡ ግራ ፡ ባጋቡ ፡ ቀስቃሽ ፡ አስተማሪዎች ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ቋንቋውን ፡ ተጠቃሚ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወገኖቻችን ፡ አሥበውና ፡ አርርመው ፡ ሊያስተካክሉት ፡ ይገባል ። ይህን ፡ ያልንበትም ፡ ምክንያትአችን ፣ **ጋልላ** ፡ ተናጋሪው ፡ ሲሆን ፡ **ኦሮሞ** ፡ ቋንቋው ፡ ነው ። በተለምዶብ ፡ ግን ፡ ጋልልኛ ፡ ስንለው ፡ ሮረናል ።

**ለምሣሌም፦** አፋ ፡ ኦረሞ ፡ ቤክታ ፤ (የኦሮሞኛ ፡ ቋንቋ ፡ ትናገራለህ ፡ ወይ?) ይላሉና ፡ ነው ። በበልለጠ ፡ ደግሞ ፡ ተቼበት ።

እንደ ፡ አቶ ፡ ኢብሳ ፡ ጉታማ ፡ ያልሉት ፡ ከዚህ ፡ በሰላምና ፡ ጤና ፡ ተቀምጠዋል ። በአገር ፡ ቤት ፡ ኗሪ ፡ ወገኖቻችንን ፡ ግን ፡ በቋንቋቸውና ፡ በዘር ፡ እያመካኙ ፡ የገንዘብ ፡ መሰብሰቢያም ፡ አድርገዋቸዋል ። ቋንቋችንን ፡ እየተጠቀምን ፡ በኢትዮጵያዊነታችን ፡ አትግቡብን ፡ የሚሉትን ፡ ሕዝቦች ፡ እኛ ፡ ነን ፡ የምናውቅላችሁና ፡ እንደ ፡ ኤርትራ ፡ ተገንጠሉ ፡ በማለት ፡ ለሥቃይና ፡ ችጋር ፡ እየዳረጓቸው ፡ ነው ። ዓለማት ፡ ከቀዝቃዛው ፡ ጦርነት ፡ ገሸሽ ፡ ባሉበትም ፡ ወቅት ፡ “ቅንጅት ፡ ድርጅታችን ፣ ኃይሉ ፡ መሪያችን” ፤ ብለው ፡ እየዘምመሩ ፡ በኢትዮጵያዊነታቸው ፡ በልጽገው ፡ ሰላምን ፡ ለማስፈን ፡ ቆርጠው ፡ የተነሡትን ፡ ለባርነትና ፡ መከፋፈል ፡ እየዳረጓቸው ፡ ነው ። ለትግራይ ፡ ኤርትሬ ፡ አምባገነን ፡ ወያኔም ፡ ስላመቻቹለት ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ እያጋጨ ፡ በማፍፋጀት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እናም ፡ ሕዝብን ፡ አስተባብሮና ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማጽናት ፡ ምቹ ፡ ስለሆነ ፡ ስሕተትን ፡ አርርሞ ፡ በመተባበር ፡ እንዲታገል ፡ ለአቶ ፡ ኢብሳ ፡ ጉተማ ፡ እናሳስባለን ። ፍቅር ፡ እንጅ ፡ ጥላቻ ፡ የትም ፡ አያደርስም ።

በሁለተኛ ፡ ደረጃም ፡ አቶ ፡ ኃይለ ፡ ልዑል ፡ ግርማ ፣ ከዋሽንግተን ፡ ዲ.ሲ.“የእነ ፡ ዶ/ር ፡ ብርሃኑና ፡ የወይዘሮ ፡ ብርቱካን ፡ ቡድን ፡ ያልተሳካው ፡ ድብቅ ፡ ተልዕኮ” ፡ ስለሚለው ፡ በጥሞና ፡ ከልሰው ፡ እንዲያስተካክሉት ፡ እና

ሳስባለን ። ያልተሳካው ፡ ሲሉ ፡ የቅንጅትን ፡ መሪ ፡ ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውልን ፡ ለመፈንቀል ፡ የታሠበው ፡ ቢከሽፍም ፡ ቅንጅትን ፡ በመከፋፈልና ፡ የውሸት ፡ ወሬ ፡ እያካሄዱ ፡ ስለሆነ ፡ ደጋፊዎችን ፡ እየጐዳን ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አቶ ፡ ብርሃነ ፡ መዋና ፡ አንዳርጋቸው ፡ ጽጌ ፡ በቅንጅት ፡ ስም ፣ ዓርማና ፡ በክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ ምሥል ፡ እየነገዱ ፡ ናቸውና ፡ ተቃውሞአችንን ፡ እንቀጥል ። የቅንጅት ፡ መማክርት ፡ ቻርተር ፡ በሚል ፡ ተለጣፊ ፡ መልእክት ፡ እያስተላለፉ ፡ ስለሚረብሹን ፡ ማስቆምም ፡ አልለብን ።

ስለ ፡ አቶ ፡ ብርሃነ ፡ መዋም ፡ የተነተኑት ፡ አሻሚ ፡ አገላለጽ ፡ ጎጃሞችን ፡ አሳዝኗል ። ይኸ ፡ እንዳይሆን ፡ በመስጋት ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ "ብርሃነ ፡ መዋ ፡ አፍሮ ፡ አሳፈረን" ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ለሌሎችም ፡ አርኣያ ፡ ለመሆን ፡ ጭምር ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቀን ፡ አብራርተንም ፡ ነበረ ። የዚህ ፡ የእርስዎ ፡ አጻጻፍም ፡ አቶ ፡ ደምመላሽ ፡ ከልክሌ ፡ እንዳሉት ፡ ድጋሚ ፡ በመሆኑ ፡ አሁንም ፡ ብርሃነንና ፡ ሌሎች ፡ ግለሰቦችን ፡ እንጂ ፡ ጎጃምንና ፡ ሕዝቡን ፡ ስለማ ይመለከት ፡ "በአካባቢ ፡ ልጅነት" ፡ የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ እንዲያርሟቸው ፡ እናሳስባለን ። ሸዋ ፣ ጎጃሜ ፡ ወዘተ.....ያሉትን ፡ ማለት ፡ ከፈልለጉ ፡ ሸዌ ፡ ጎጃሜ ፡ ወይም ፡ ሸዋ ፣ ጎጃም ፡ ወዘተ....ይበሉት ። ለምን ፡ ቢባል ፡ አገሮችንና ፡ ሕዝቦችን ፡ ለመለየት ፡ ነው ። በአካባቢ ፡ ልጅነት ፡ የሚለውን ፡ የተቃወምንበትም ፡ ምክንያት ፡ እነ ፡ ዶ/ር ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋ ፣ ወይዘሮ ፡ ብርቱካን ፡ ሚዴቅሳ ፣ ታማኝ ፡ በየነ ፣ አንዳርጋቸው ፡ ጽጌ ፡ ወዘተ....የአካባቢ ፡ ልጅነት ፡ የልላቸውም ። ቅንጅትን ፡ ከፍለው ፡ የወገኑትም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋራ ፡ ስለሆነ ፡ ይታሰብበት ። ዋናው ፡ ዓላማቸውም ፡ የጥቅም ፡ ስስታሞች ፡ እንጂ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አንድነት ፡ በማሰብ ፡ አይደለም ፡ ብለን ፡ ገምተናል ። "የሲያትሉ ፣ የዲሲው ፣ የቶሮንቶው ፣ የካልጋሪው ፣ የአትላንታው" ፡ ወዘተ... ስለተባሉትም ፡ በገንዘብ ፡ የደለሏቸው ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ። አጋጣሚም ፡ ስለሚሆን ፡ በሚገባ ፡ አጣርቶ ፡ መጻፉ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። የመቅጠርና ፡ የመቀጠርም ፡ መብት ፡ ስላላቸው ፡ መጠንቀቅ ፡ ያስፈልጋል ። የእኛም ፡ ቅርሬታ ፡ ቅንጅትን ፡ ለመከፋፈል ፡ መሣሪያ ፡ በመሆናቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። በግል ፡ አስተያየታችንም ፡ ቅንጅትንና ፡ መሪውን ፡ እንዳናስወቅስ ፡ አደራ ፡ እንላልለን ። ብዙ ፡ ሥራ ፡ ስላለብን ፡ ከእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ በዘር ፡ ከፋፋይ ፡ አጻጻፍ ፡ መታቀቡ ፡ ጠቃሚ ፡ ይመስለናል ። አለበለዚያማ ፡ እኛው ፡ ከምናወግዘው ፡ የትግራይ ፡ ኤርትሬ ፡ አምባገነንና ፡ ዘረኛ ፡ ወያኔ ፡ በምን ፡ እንለያልለን? ።

## ድል ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለሕዝቧ!!!

ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፳፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።